የሰ/መ/ቁ. 56368

ህዳር 1 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፣** ሐጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች -** ዶ/ር ሰሎሞን ነጋሽ ዶ/ር ዘውድነህ በየነ ቀረበ

**ተጠሪ -** የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ሙላት ያዛቸው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ ሰበር ችሎት እንዲወሰን ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ቀደም ሲል በተደረገው ውል መሠረት የግልግል ዳኛ በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲመረጥ አመልካች አቅርቦት የነበረውን ጥያቄ የሚመለከት ነው አመልካች ጥያቄውን ያቀረበው ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ፍ/ቤቱ ተጠሪን አስቀርቦ መልስ እንዲሰጥ ከማድረጉ በፊት ጥያቄው በፍ/ቤት የሚስተናገድ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 231 የተመለከተውን ድንጋጌ በመጥቀስ መዝገቡን ዘግቶአል ጉዳይ በይግባኝ የቀረበለት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤትም ይግባኝ የተባለበት ትዕዛዝ ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 14 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው ለአመልካች ክስ መሠረት የሆነው በሁለቱ ወገኖች መካከል የተደረገ ውል መሆኑ እስካላከራከረ ድረስ እንደውሉ ጉዳዩ በግልግል ያልቅ ዘንድ የፍ/ቤትን እገዛ በመጠየቅ የቀረበው ክስ በማያስከስስ ነገር ላይ የቀረበ ነው በማለት ሳይስተናገድ የመቅረቱን አግባብነት ለመመርመር ነው በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ትዕዛዝ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለጸው አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረተው በመሃከላቸው የተደረገውን ውል መነሻ በማድረግ ነው ውሉ ነሐሴ 28 ቀን 2000 ዓ.ም የተደረገ የማማከር አገልግሎት የመስጠት እንደሆነም በክርክሩ ተመልክቶአል በሌላ በኩል ደግሞ የውሉን አፈፃፀም በሚመለከት በመሃከላቸው አለመግባባት ቢፈጠር እና አለመግባባቱን በድርድር መፍታት ካልተቻለ ሁለቱ ወገኖች በሚያቋቁሙት የግልግል ዳኝነት እንደሚታይ ስምምነት ስለመደረጉ ግራቀኝ ወገኖች አልተካካዱም አመልካች ወደክስ ያመራው ተጠሪ በውሉ መሠረት ለመገዛት ፈቃደኛ አልሆነም

በማለት ሲሆን የጠየቀው ዳኝነትም ተጠሪ በውሉ በገባው ግዴታ መሠረት የግልግል ዳኛ እንዲመርጥ ይገደድልኝ የሚል ነው፡፡

እንደሚታየው አመልካች እና ተጠሪ በመሃከላቸው ያቋቋሙትን መብት እና ግዴታ የሚገዛ ውል አድርገዋል፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁ 1731 እንደተደነገገው በሕጉ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ባቋቋሙዋቸው ሰዎች ላይ ሕግ ናቸው ከሣሽ የሆነው ወገን ተጣሰብኝ የሚለውን መብት ለማስከበር ዳኝነት የሚጠይቀው የመብቱን ምንጭ ወይም መሠረት ውል ወይም ህግ እንደሆነ በማረጋገጥ ስለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 33/2/ አነጋገር ከሣሽ ከተከሣሽ ላይ የሚጠይቀውን ጥቅም ወይም መብት በማረጋገጥ አቤቱታውን ያቀርብ ዘንድ ይጠበቅበታል ሲባልም የመብቱ መሠረት ሕግ ወይም ውል መሆኑን በግልጽ ማሳየት አለበት ማለት ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ተጠሪ ይፈጽምልኝ የሚለው ግዴታ መሠረቱ ውሉ እንደሆነ አሳይቶአል ተጠሪም ለአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰጠው መልስ እንደገለጸው ስለውሉ መደረግም ሆነ ስለይዘቱ የሚክደው ነገር የለም፡፡ ክርክሩ ተከሣሽ የመንግስት መሥሪያ ቤት በመሆኑ ጉዳዩን በግልግል እንዲጨርስ በሕግ አይገደድም የሚል እንደሆነም ከዚሁ መልሱ ይዘት ተገንዝበናል፡፡

ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የክሱን መዝገብ የዘጋው ተጠሪን ሳያስቀርብ እንደሆነ ከላይ ተገልጾአል፡፡ መዝገቡን ሊዘጋ የቻለውም አመልካች የክስ ምክንያት የለውም በማለት ነው ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፍ/ቤትም በተመሳሳይ ሁኔታ ይግባኙን ሰርዞአል በመሆኑም ይህ የሰበር ችሎት በዚህ ደረጃ ሊያይ የሚገባው አመልካች ያቀረበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም በማለት የተሰጠው ትዕዛዝ አግባብነት ያለው ነው ወይ? የሚለውን ጭብጥ በመሆኑ ተጠሪ በግልግል ዳኝነት ጉዳዩን እንዲጨርስ የሚለውን የሥረ ነገር ክርክር የምንመረምርበት አግባብ የለም፡፡ ወደያዝነው ጭብጥ ስንመለስም አመልካች በክሱ ላይ የገለጸው ጉዳይ /ነገር/ የክስ ምክንያት የሌለው /የማያስከስስ/ ነው የሚባል ባለመሆኑ አቤቱታ የቀረበበት ትዕዛዝ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ 39576 ሚያዚያ 21 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና በአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ 29491 ግንቦት 12 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ውሉን መሠረት በማድረግ ያቀረበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም በማለት ሳይስተናገድ መቅረቱ በአግባቡ አይደለም ብለናል፡፡ ስለዚህም የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱን ለተጠሪ እንዲደርስ በማድረግ እና ግራቀኝ ወገኖች በክሱ ስረ ነገር የሚያቀርቡትን ክርክር ከሰማ በኃላ ተገቢውን ይወሰን ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 341/1/ መሠረት ወስነናል፡፡
3. ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት